NAFYAD SCHOOL

1 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 1ST LAGUAGE 1

መመሪያ አንድ

ከተራ ቁጥር **1-5** ለተሰጡት ቃላት ይበልጥ የሚመሳሰል መልሳቸውን በመምረጥ መልስ መስጫውን ወረቀት ላይ አጥቁር/ሪ/

1. ሀሴት

A. ትዕቢት B. ቀጠሮ C. የመጀመሪያ D. ደስታ

2. አመላካች

A. አመለካከት B. ጠቋሚ C. አቤቱታ አቅራቢ D. ፊፃሚ

3. ቋያ

A. ችቦ B. ፍም C. ሰደድ እሳት D. መንደር

4. ገደብ

A. መከላከያ B. ቦታ C. ወሰን D. መልሱ አልተሰጠም

5. ትስስር

A. ቁርኝት B. ጭቅጭቅ C. ምልልስ D. ውይይት

መመሪያ ሁለት

ከተራ ቁጥር **6-10** ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒያቸውን በመምረጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን የመልስ ሆሄ አጥቁር/ሪ/

6. ታዳጊ

A. አዳኝ B. ተስፈኛ C. አጥፊ D. ለጋ

7. ደነገገ

A. አፀደቀ B. ወሰነ C. ሻረ D. አመለካተ

8. ብስራት

A. ደስታ B. የምስራች C. መርዶ D. ፈገግታ

9. ጎላ

A. ደመቀ B. ካሳ C. ደበዘዘ D. ወፈረ

10. ተዛባ

A. ተወላገደ B. ተስተካከለ C. ተጣመመ D. ተላለፈ

መመሪያ ሶስት

ከተራ ቁጥር **11-15** ለተሰጡት ፊሊጣዊ አነጋገሮች ትክክለኛውን /ፍቺ/መልስ የሆኑትን መርጠህ/ሺ/ትክክለኛውን የመልስ ሆሄ አጥቁር /ሪ

11. ምላጭ አፍ A. የማይናገር B. ሆድ ቆራጭ C. አታላይ D. ተናካሽ

12. ረጋ-ሰራሽ

A. በርጋታ የተሰራ B. በዕውቅ የተሰራ C. የተጠናከረ ስራ D. የለማጅ ስራ

13. እምብርት የለሽ

A. ቦርጫም B. የማይጠግብ C. የማያስብ D. የማያዝን

14. ቃል አባይ

A. ውሸታም B. ዳተኛ C. መሰሪ D. ቃሉ የታመነ

15. የደም ገንቦ

A. ቆንጆ B. ማሰሮ C. የደም መቅጃ D. ወፍራም

መመሪያ አራት

ከተራ ቁጥር **16-20** ከቀረቡ አማራጮች ውስጥ ልዩ የሆነውን ወይም ከቀረሩት የማይመሳሰለው ቃል በመምረጥ የመልስ ሆሄውን አጥቁር ወይም አጥቁር

16 . A. ደሴት B. ሀይቅ C. ባህር D. ኩሬ

17. A. ዳዋ B. ሜዳ C. አረም D. ጢሻ

18. A. ባልንጀራ B. ባልደረባ C. ጓደኛ D. ባላንጣ

19. A. ቁም ነገር B. ቧልት C. ቀልድ D. ፌዝ

20. A. መርህ B. ድርጊት C. ስራ D. ተግባር

መመሪያ አምስት **:-** ከዚህ በታች የተሰጠውን ምንባብ አንብበህ/ሽ/ከግጥሙ ውስጥ ለወጡት ከ **21-25** ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር መልስ/ሺ/

የተፈጥሮ ሀረግ የሰዎች ሰንሰለት፣

በፅንሰት ውጣኔ ነፍስ የሚጋሩበት

በረከት ነው ሚስጥር ልዩ ነው ትርጉሙ፣

የእናትነት ድርሻ ፍቅራዊ ጣዕሙ።

በልዩ ቁርኝት ስጋ ነፍስ ተካፍሎ፣

አንዱ በሌላ ውስጥ በተአምር በቅሎ

በድንቅ ህላዊ ግብሩ በረቀቀ፣

1 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 1ST LAGUAGE 1

የሚታይ ዝምድና ከሁሉም የላቀ።

ልጅነት በረከት እናትነት ፀጋ፣

ይህ ፍቅር ውድ ነው በተፈጥሮ ዋጋ።

የስሜቱን ባህሪ ገመና ውስጠቱን፣

ውህደት አንድነቱን ፅናቱን ጥልቀቱን፣

በእርካታው መጠን መስዋእትነቱን፣

የእናት መሆንን ወግ ህይወትን መስጠቱን።

የተባ አገላለጽ የሀሳብ ትንታኔ፣

ገልጾ አይጨርሰውም የመጠቀ ቅኔ።

‹‹የስሜት ትኩሳት›› ከፀሐፌ መላኪ

የግጥም መድብል የተወሰደ

21. ውድ የተፈጥሮ ዋጋ የተባለው ምንድነው?

A. የእናትነትና የቤተሰብ ፍቅር B. የሀገር ፍቅር

C. የእናትነትና የልጅ ፍቅር D. የተፈጥሮ ፍቅር

22. በተሰጠው ግጥም በበለጠ ርዕስ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው ?

A. የልጅ በረከት B. እናትነት C. የተፈጥሮ ፀጋ D. የሀገር ፍቅር

23. የቀረበው ግጥም ስንት ስንኞች አሉት? A. 32 B. 8 C. 24 D. 16

NAFYAD SCHOOL

1 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 1ST LAGUAGE 1

24. ግጥሙ ስንት አንጓዎች አሉት? A. 14 B. 7 C. 8 D. 16

25. የተባ የሚለው ቃል ምንን ይገልፃል?

A. የላቀ B. ግልፅ የሆነ C. የነተበ D. አደናጋሪ

መመሪያ ስድስት

ከተራ ቁጥር 25-30 ለተጠየቁት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በመጠየቁ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ/

26. ሁበረት ሀይል መሆኑን የሚያሳየው ምሳሌያዊ አነጋገር የቱ ነው?

A. ለሃምሳ ጋን አንድ አሎሎ B. ለሺ ፍልጥ ማስሪያው ልጥ

C. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር D. ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም

27. <u>ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ</u> ። ለሚለውን አነጋገር የበለጠ የሚገልፀው የቱ?

A. ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ B. ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ

C. ሞኝ የእለቱን ብልህ የዓመቱን D. የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች

28. <u>እርሾው ሲያምር ዳቦው ያምር</u> ። የበለጠ የሚመሳሰለው

A. አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ B. እናቷን አይተህ ልጆቹን አግባ

C. ጅብ የማይታወቅበት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉ አለ D. ደባ ራሱን ስለት ደግሱን

29. ---------- ይዞ ፀሎት፣ሳል ይዞ ስርቆት በባዶው ቦታ የሚገባው ቃል የቱ ነው

A. ፀፀት B. ቂም C. በረከት D. ልመና

30. ማን ይናገር የነበረ፤ ---------። በባዶ ቦታ ገብቶ አባባሉን በትክክል የሚያሟላ የቱ ነው?

A. ማን ይመሰክር ያማተረ B. ማን ይፍረድ ተሰየመ

C. ማን ይሂድ የሰነቀ D. ማን ያርዳ የቀበረ

መመሪያ ሰባት

ከ **31-45** ለቀረቡ የቋንቋ ነክ ጥያቄዎች በመጠይቁ መሰረት ትክክለኛ የሆኑትን በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀትህ ላይ አጥቁር/ሪ/

31. ትክክለኛ የሆነውን የዘመድ/የጓደኛ / የደብዳቤ አፃፃፍ አካላት/ቅደም ተከተል የያዘው ምርጫ የቱ ነው?

A. ሰላምታ፣ ቀን፣ የላኪ አድራሻ፣ ስምና ፊርማ

B. ቀን፣የላኪአድራሻ፣ ሰላምታ፣ ሀተታ /ፍሬ ነገር/፣ መዝጊያ ስምና ፊርማ

C. ሰላምታ ፣ቀን፣ የላኪ አድራሻ፣ ስምና ፊርማ፣ መዝጊያ

D. መዝጊያ፣ቀን፣ሀተታ፣የላኪ አድራሻ፣ ስምና ፊርማ

32. ‹‹ለምኖ መኖርን የመሰለ ክብር የለም»። የሚለው አነጋገር የትኛውን የዘይቤ ዓይነት ያሳያል?

A. አያዎ B. ምስያ C. ግነት D. ምፀት

33. ጠበሰ ብሎ መጠባበሻ ቢል ፈነከተ ብሎ ------ ይላል።

A. መፈንከቻ B. ፈነከተ C. መፈነካከቻ D. ፈንካች


34. ችግኝ ተከለ ቢል ጤፍ -------- ይላል። A. ረጨ B. በተነ C. አቦካ D. ዘራ


NAFYAD SCHOOL


1 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 1ST LAGUAGE 1


35. በአንቀፅ ውስጥ ሀይለ ቃል መጨረሻና መጀመሪያ ላይ የሚመጣ ከሆነ የሀሳብ አካሄዱ የትኛውን ቅርጽ

ይይዛል?

A. 

B. 

C. 

D. 

36. ዓለምነሽ ከ ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ አምስተኛ ስለወጣች አራት ተማሪዎች በልጠዋታል።

በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ ደረጃ አመልካች ቁጥር የሆነው የቱ ነው?

A. ሰባተኛ B. አምስተኛ C. አራት D. A እና B መልሶች ናቸው

37. <u>‹‹ሰደረ››</u> እና <u>‹‹ደረሰ››</u> የሚሉት ቃላት መካከል የፍቺ ለውጥ ሊመጣ የቻለው በምን ምክንያት ነው።

A. በአናባቢዎች መለያየት የተነሳ B. በተነባቢዎች መለያየት የተነሳ

C. በድምፆች ውህደት የተነሳ D. በድምፆች ቦታ መለዋወጥ የተነሳ

NAFYAD SCHOOL

1 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 1ST LAGUAGE 1

38. እየመጡ ነው። የተሰመረበት ቃል የሚያመለክተው

A. እሱን B. እነሱን C. እሳቸውን D. A እና C መልሶች ናቸው

39. በውይይት ወቅት ለቤቱ መነጋገሪያነት የቀረቡ ርዕሶች ምን ይባላሉ ?

A. ቃለ-ጉላኤዎች B. አጀንዳዎች C. ምልዐተ ጉባኤዎች D. አፈ ጉባኤዎች

40. ብርን እና ሳንቲምን ለመለየት የሚያገለግለው ስርዓተ-ነጥብ የቱ ነው?

A. ይዘት B. ነቁጥ C. ነጠላ ሰረዝ D. እመጫት

41. ድርብ ቃል የሆነው የቱ ነው?

A. ስለዚህ B. ቀስተ ደመና C. መስቀለኛ D. ሁሉም መልሶች ናቸው

42. በአንቀፅ ውስጥ ሌሎች ዐ.ነገሮች የያዙትን ሀሳብ አጠቃሎ የያዘው ዐረፍተ ነገር ምን ይባላል?

A. ምህዳረ ቃል B. ሀይለ ቃል C. ድርብ ቃል D. አቢይ ቃል

43.ተለጣጣቂነት ያላቸው የግጥም ቃላት ቅንብሮች የሚያስገኙት ስርዐታዊ የድምፅ ፍሰት /አወራረድ/------- ይባላል።

A. ምት B. አንጓ C. ምጣኔ D. ዜማ

44. ከሚከተሉት ውስጥ ከስነ-ቃላዊ ግጥም ውጭ የሆነው የቱ ነው?

A. እቱ አበባሽ ስትለኝ ከርማ B. ከቤት በላይ ቁራ ሰፍሮ፣

NAFYAD SCHOOL

1 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 1ST LAGUAGE 1

ትታኝ ሂደች በሀምሌ ጨለማ የለችም ብሎ በሮ በሮ

እኔን ያብረኝ ያክንፈኝ

የዝሆን አሞት ያስጠጣኝ

C. ተሞተና ተለቀሰ፣ D. ያንን ድግስ ውጪ ውጪ

እንባ እንደ ጅረት ፈሰሰ፡ በድንክ አልጋ ተገልብጬ

እንዲሁ እንደዋተተ፣ ያቺ አልጋ አመለኛ

ኗሪ ሳይኖር ሞተ ያለ አንድ ሰው አታስተኛ

45. ጀግና ነህ ይላሉ የታል ጀግንነትህ ፣

ሴት በፈተለችው የታሰረው ጣትህ ። ይህ ስነ-ቃሉ የሚነገረው በ--------- ጊዜ ነው።

A. በፉከራ B. በሙሾ C. በአጨዳ D. በቀረርቶ

መመሪያ አምስት

ከተራ ቁጥር 46-48 ለተሰጡ ዐ.ነገር ላይ ያተኮሩ ጥያቄዎችን አጥብበህ /ሽ/በመጠይቁ መሰረት ትክክለኛውን መልስ አጥቁር/ሪ/

46. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የተቀመጡት ዐ.ነገሮች ተቀናጅተው አንቀፅ ሲመሰርቱ የዐ.ነገሩ ቅደም ተከተል የቱን ይሆናል።

ሀ. ስለዚህም ነበር ምስጢር ያውቁና ግዕዝን አጣርተው ይናገሩ የነበረው።

ለ. በተወለዱበት በጌምድር ደብረ ታቦር ባለው የኢየሱስ ደብር ዳዊትን ተከታትለው ሲያበቁም ትምህርት እውቀት

በቃኝ ብለው አልተቀመጡም።

ሐ. ቀለም የጠማቸው ነበሩና ሌሎች እውቀት ይሰጡ የነበሩትን የሀይማኖት ትምህርቶች በታወቁ አድባራት

እየተዘዋወሩ ከታወቁ ሊቃውንት ቀስመዋል።

መ. ያየኔው ዘመን ዘፈን «ሔዋን ተምራ ጋራ አትግፉም» የሚል ግጥምን ቢይዝም ዕድሜ ለቤተሰቦቻቸው ጣይቱ ቡጡል

ዳዊትን አሳምረው ያውቁታል።

A. መ፣ለ፣ሐ፣ሀ B. መ፣ለ፣ሀ፣ሐ

C. ሐ፣መ፣ለ፣ሀ D. ለ፣ሀ፣መ፣ሀ

47. ወደ፣ባሌላ፣ታክሲ፣ቦሌ፣አመራሁ። እነዚህን ቃላት በትክክል በማቀናጀት የሚመሰረተው አረፍተ ነገር የቱ ነው?

A. ወደ ታክሲ አመራሁ በሌላ ቦሌ B. በሌላ ታክሲ ወደ ቦሌ አመራሁ።

C. አመራሁ በሌላ ታክሲ ወደ ቦሌ D. ወደ በሌላ ቦሌ አመራሁ ታክሲ

NAFYAD SCHOOL

1 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 1ST LAGUAGE 1

48. በትክክል የተፃፈው አረፍተ -ነገር የቱ ነው?

A. የሚማረው በጅማ ዩኒቨርስቲ ነው ልጁ። B. ልጁ የሚማረው በጅማ ዩኒቨርስቲ ነው።

C. በጅማ ነው ዩኒቨርስቲ የሚማረው ልጁ D. የሚማረው ልጁ በጅማ ዩኒቨርስቲ ነው።

መመሪያ ዘጠኝ

49-52 ለተሰጡት ሰዋሰዋዊ እና ስነፅሁፋዊ ጥያቄዎች ተስማሚ የሆነውን መልስ በመምረጥ አጥቁር/ሪ/

49. ታሪክን በጊዜ፣ በቦታ ወይም በድርጊት ቅደም ተከተል የሚገልፅ የድርሰት ዓይነት የቱ ነው?

A. አመዛዛኝ ድርሰት B. ገላጭ ድርሰት C. ተራኪ ድርሰት D. አከራካሪ ድርሰት

50. <u>አበበ ድመቱን ዘወትር ይመግባታል</u>። ከተሰመረበት ዐ.ነገር ውስጥ ትክክለኛው የቱ ነው?

A. አበበ ግስ ፤ ድመቱን ተሳቢ ይመግባታል ግስ B. አበበ ባለቤት፤ድመቱን ተሳቢ፤ ይመግባታል ግስ

C. ይመግባታ፣ ባለቤት ፣ድመት ተሳቢ ፣ አበበ ግስ D. መልሱ አልተሰጠም

51. <u>አየሩ ስለታፈነ መስታወቱን ከፈቱት</u>። የተሰመረበት ዐ.ነገር የቱን ይሆናል?

A.መጠይቅ ዐ.ነገር B. ሀተታዊ አረፍተ ነገር C. ትዕዛዛዊ ዐ.ነገር D. አጋናኝ ዐ.ነገር

52. ዝናቡ እየዘነበ ነው።---------- የእግር ኳስ ጨዋታው ቀጥሏል በባዶው ቦታ የሚገባው አያያዥ ቃል የቱ ነው?

A. ስለዚህ B. ስለሆነም

C. ነገር ግን D እና

መመሪያ አስር

ከዚህ ቀጥሎ የተሰጠውን ምንባ አንብበህ/ሽ በምንባቡ መሰረት ከ **53-57** ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ አጥቁር/ሪ/

ፎረፎር ቀላል የቆዳ ችግር ቢሆንም በንፅህና ጉድለት ወደ ከፋ የቆዳ በሽታ ሊዛወር ይችላል።አብዛኛውን ጊዜ ፎሮፎር የሚከሰተው በወጣቶች ላይ ሲሆን ዕድሜ እየጨመረ ሲሄድ ፎሮፎር እየቀነሰ ሊሄድ ይችላል።

ፎሮፎር የሚከሰተው ወዝን ከሚያፈልቁ ንጥረ ነገሮች መከሰት ጋር ነው። ውስጣዊ በሽታ ያለባቸው፤ አልኮልን አዘውትረው የሚጠጡና የአዕምሮ ቁጡነት ያለባቸው ሰዎች ለፎሮፎር ችግር የተጋለጡ ሊሆኑ ይችላሉ።

ከወዛምነት ጋር አብሮ ሊያያዝ የሚችለው ሌላው ጉዳይ በቆዳችን ላይ ብዙ የፈንገስ ዘሮችም በሰውነታችን ላይ ይገኛሉ። እነዚህን የፈንገስ ዘሮች በተለይ በቆዳ ላይ ወዝ በሚኖርበት ጊዜ በጣም ይራባሉ። ወዙን እንደ ምግብ ይጠቀሙበታል ና።

አብዛኛውን ጊዜ ፎሮፎር ከራስ ቅል ጋር ብቻ እናያይዘዋለን ። ይሁንና አፍንጫ አካባቢ ቅርፊት የመያዝ ሁኔታ፣የቆዳ ቀዳዳዎች ከፍ ከፍ ማለት ፣የአይን ቅንድብ ፣ አንገትና ደረት ላይ ቅርፊት የመያዝ ነገርም የሚመደበው ከፎሮፎር ነው።

በራስ ቅል ላይ ያለ ቅርፊት ሁሉ ፎሮፎር ነው ብሎ ለመደምደም አያስደፍርም ፎሮፎር ያልሆነና በራስ ቅል ላይ የሚከሰትም በሽታ አለ። ይህ በሽታ እየተባባሰ ከሄደና ለረጅም ጊዜ ቅርፊቱ እየተጠናከረ ከሄደ ሌላ

NAFYAD SCHOOL

1 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 1ST LAGUAGE 1

በሽታ ሊሆን ስለሚችል መመርመር ያስፈልጋል። ፎሮፎር ም ቢሆን በጣም ካስቸገረ ፣ቅርፊቱ እየበዛና ማሳከኩ እየጨመረ ከሄደ የግድ ሐኪምን ማማከር ተገቢ ይሆናል።

ከቀድሞ **7** ኛ ክፍል የተማሪው

መፅሐፍ ተቀንጭቦ የተወሰደ

53. ስለ ፎሮፎር ትክክል የሆነው የቱ ነው?

A. ቀላል ቢመስልም ወደ ከፋ የቆዳ በሽታ ይለወጣል።

B. እየተባባሰ የሚሄደው በንፅህና ጉድለት ነው።

C. ወዝ ከሚያፈልቁ ንጥረ ነገሮች ይከሰታል ።

D. ሁሉም መልሶች ናቸው።

54. ከሚከተሉት ውስጥ በፎሮፎር የማይጠቃው የአካል ክፍል የቱ ነው?

A. አፍንጫ B. የቆዳ ቆሻሻዎች C. አንገትና ደረት D. የውስጥ እጅ

55. ለፎሮፎር በሽታ ተጋላጭ የሆኑት የህብረተ-ሰብ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው።

A. የግል ንፅህናቸውን የማይጠብቁና ወጣቶች B. አልኮል አዘውትረው የሚጠጡ ሰዎች

C. ውስጣዊ በሽታ ያለባቸው ሰዎች D. ሁሉም መልሶች ናቸው።

56. ለፎሮፎር ፈውስ መንስኪነት የተጠቀሰበት አንቀፅ የትኛው ነው?

A. አንቀፅ አምስት B. አንቀፅ አራት C. አንቀፅ ሶስት D. አንቀፅ አስር

57. ምንባቡ ስንት አንቀጾች አሉት?

A. አምስት B. አራት C. ሦስት D. አንድ

መመሪያ አስራ አንድ

ከ **58-60** ላሉት የቅኔ ጥያቄዎች በመጠይቁ መሰረት ትክክለኛውን መልስ መርጠህ/ሽ/ አጥቁሪ/ር/

58. ለነገ ቅዳሴ ጧፍ ማጦፍ አለብኝ፣

ያቺ ያገሬ ልጅ ሰምታ መጣችልኝ። <u>የቅኔው ህብረ -ቃል የቱ ነው**?**</u>

A. ሰምታ መጣችልኝ B. ለነገ ቅዳሴ C. ማጦፍ አለብኝ D. ያቺ ያሬ ልጅ

59. ማር ቀምሼ አላውቅም እኔ ወንድማችሁ፤

ያገሬ ወጣቶች ተማሩ እባካችሁ። <u>የቅኔው ሰም ትርጉም የሚሆነው የቱ ነው**?**</u>

A. እኔ ወንድማችሁ ማር እወዳለሁ B. ለወጣቶች ማር ይስማማቸዋል

C. ወጣቶች እባካችሁ ዕውቀትን ቅሰሙ D. ያገሬ ወጣቶች ለኔ ማር ስጡኝ

60. ዘቢቡን ገዝቼ ይዤ ስጠበቀው፤

ቁሱ እጣኑን ወስዶ ካፊር ደባለቀው ። <u>ከቀረቡት አራት አማራጮች ወርቅ ትርጉሙን የሚያመለክተው የቱ ነው**?**</u>

A. ለፀሎት የመጣውን ዕጣን ቁሱ ደፋው B. ቁስን መጠበቅ ዘቢብና እጣን ይዞ ነው

1 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 1ST LAGUAGE 1

C.እጣኑና አፈሩ አብሮ ጨሰ D. ህፃኑን ልጅ የቀበረው ቄሱ ነው።

NAFYAD SCHOOL

1 SAMPLE MODEL EXAM. FOR GRADE 8 AMHARIC 1ST LAGUAGE 1